# DEBRE BERHAN UNIVERSITY ELECTRICAL AND COMPUTER ENGINEERING STUDENTS ASSOCIATION

## በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና የተማሪዎች ማህበር

ቁጥር

**RfNo/DBUECESA/------/-----**

ቀን----------------------------------

ለ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ምህንድስና ኮሌጅ

ለ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና ትምህርት ክፍል

ለ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ህብረት

ደብረ ብርሃን

ጉዳዩ ፦ <u>ቅሬታ ማቅረብ ይመለከታል።</u>

የኮሮና ቫይረስ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና ስጋት መሆኑ ይታወቃል።በአሁኑ ጊዜ የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከልና ለመግታት መንግስት መጠነ ሰፊ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። የዓለም የጤና ድርጅትም በሽታው ወረርሽኝ መሆኑን ካወጀበት ጊዜ አንስቶ ለጥንቃቄ ይጠቅማሉ ብሎ ካስቀመጣቸው መፍትሄዎች መካከል የሰዎች መሰባሰብን የሚሹ ጉዳዮችን ማስቀረት በዋናነት ይገኝበታል።የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የመጡ በመኾናቸው ተቋማቱን ዘግቶ ተማሪዎቹን ወደየቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ቫይረሱ እንዳይስፋፋ ስለሚያደርግ ተቋማቱ ተዘግተዋል።

ስለሆነም ደብረብርሃን ዩንቨርስቲ በወረሽኙ መስፋፋት ስጋት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይቆራረጡ ባሉበት ሆነው የመማር ማስተማሩ ስራ በኦላይን እንዲሆንና ተማሪዎች በቤታቸው ሆነው የተሰጣቸውን **handout,portable document format(PDF),power point(ppt) materials,reference books** እና ሌሎች ማንኛውንም አጋዥ የሆኑ ነገሮችን እያነበቡና አሳይመንቶችንና የምዘና ፈተናዎችን እንዲወስዱ እስትራቴጂካዊ ዕቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።በመሆኑም አብዛኛው የአገራችን ሕብረተሰቦች የዕለት ተዕለት ሥራቸው ግብርና መሆኑ ይታወቃል።ይሕም

አገራችን ዝቅተኛ ገቢ ካላቸውና የኑሮ ድህነት ካላቸው አገሮች መካከል አንዷ ናት።በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎችን ብናይ እንኳን አብዛኞቹ ቤተሰቦቻቸው በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ናቸው።ስለሆነም ሕብረታችን በአንዳንድ ማሕበራዊ መገናኛ ብዙሃን በሚደርሱት ጥያቄዎች መሰረት የኦላይ የመማር ማስተማሩን ጉዳይ የሚከተሉት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ወደ ሕብረቱ እየመጣ ይገኛል።

**1** ኛ**.**ደብረብርሃን ዩንቨርስቲ እንዲሁም የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ለተማሪዎች አጋዥ ይሆናሉ ብሎ ያስቀመጣቸውን **digital library** እና የተለያዩ የ **website link** አስቀምጧል። ነገር ግን እኛ ተማሪዎች እነዚህን ለመጠቀም የኢኮኖሚ አቅም ስለማይፈቅድልን እና ለኢንተርኔት ለመጠቀም ለቴሌ የምንከለው ክፍያ ስለሌለን ለማንበብም ሆነ አሳይመንቶችንና ፕሮጀክቶችን ለመስራት ተቸግረን እንገኛለን።

**2** ኛ**.**በአገራችን በቆላማውና እና አንዳንድ አካባቢዎች የኢንተርኔት እና የመብራት ተደራሽነቱ ስለሌለ በዚያ አካባቢ የምንኖር ተማሪዎች በኦላይ ትምህርት ለመማር እጅግ ከባድ ሁኔታ ሆኖብናል።

**3** ኛ**.softcopy** ማቴሪያልዎችን ለማንበብ **smart phone/any digital device** የሌለን ተማሪዎች የኦላን ትምህቱን ለማስቀጠል እጅግ ከባድ ሆኔታ አድርጎብናል።

ስለሆነም የኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና የተማሪዎች ማሕበር ከላይ የቀረቡ መሠረታዊ የተማሪዎችን ጥያቄ የሕብረቱ ጥያቄ ብሎት ምላሽ እንዲሰጠው ሕብረታችን ይጠይቃል።

Email address: zelast.bird99@gmail.com የመልስ ደበዳቤዎትን በ Email አድራሻችን መላክ ይችላሉ።
Telegram channel: http//t.me/DBU_ECESA_Official phone no. 0983050637/0937411503

# DEBRE BERHAN UNIVERSITY ELECTRICAL AND COMPUTER ENGINEERING STUDENTS ASSOCIATION

በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና የተማሪዎች ማህበር

ከሰላምታ ጋር

ዘላለም ብርሃኑ

የማህበሩ ሰብሳቢ